# ለተጓዦች የወባ እውነታዎች

## የወባ በሽታ ምንድነው?

የወባ በሽታ ከቢንቢ ንክሻ የሚመጣ በሽታ ነው፡፡ ከወባ በሽታ ሊከላከሎት የሚችል ክትባት የለም፡፡ የወባ በሽታ በጣም ከባድ ሊሆን ይችላል፡፡



የወባ በሽታን ለማስቀረት የሚያስችለው ጥሩ መንገድ የቢንቢ ንክሻ ማስወገድና በጉዞ ወቅትና ከጉዞ ከተመለሱ በኋላ ከሀኪም በታዘዘው መሰረት መድሀኒቱን በአግባቡ በመውሰድ ነው፡፡ በፊት የወባ በሽታ ያለባቸው ሰዎችም ቢሆኑም እንኳ፣ የህመም ስሜት በተሰማ በ 12 ሰአታት ውስጥ ሕይወት ሊያልፍ ይችላሉ፡፡

## የወባ በሽታ ችግር የሆነው በየት ነው?

የወባ በሽታ በብዙ ሀገራት አለ፡፡ ባለ ቀይና ቢጫ ቀለማት የወባ በሽታ ስጋት ያለባቸው ሀገራት ናቸው፡፡




## በጉዞ ላይ የወባ በሽታ ሊይዘው የሚችለው ማንን ነው?



ሁሉንም ተጓዦች - ልጆችና አዋቂዎችን - የወባ በሽታ ያለበት ሀገር የሚጓዝ ሰው የታዘዘለትን መድሀኒት መውሰድና በጉዞ ላይ የቢንቢን ንክሻ ለማስወገድ መሞከር፡፡

በዙ ግዜ ያሳለፉበት ቦታ ቢሆንም እንኳን ከወባ በሽታ የተጠበቁ ሊሆኑ አይችሉም፡፡

ብዙ ግዜ ያሳለፉ ሰዎች ከወባ በሽታ የተወሰነ ጥበቃ ሊኖራቸው ይችላል ነገር ግን ጥበቃው ያለፈበት ሆኖ ይህም የወባ በሽታው ያለበት ቦታ ከለቀቁ በአንድ ወር ግዜ ውስጥ ነው፡፡ እርሶንና ቤተሰብዎን ደህንነት ሊጠብቅ የሚችለው ምርጡ መንገድ የወባ በሽታ መድሀኒትን መውሰድና ከቢንቢ ንክሻ በመጠበቅ ነው፡፡

የወባ በሽታ ህጻናትን በተለይም ሁል ግዜ ከዩኤስ የሚወጡትን በጣም ሊያሳምም ይችላል፡፡ ከዚህ በፊት የወባ በሽታ የሌለባቸው ህጻናት ወይም አዋቂዎች በታመሙ ግዜ ወዲያውኑ ሊሞቱ ይችላሉ፡፡

# ነፍሰጡር ከሆንኩስ?

ነፍሰጡር ሆነው በወባ በሽታ መያዝ እርሶንና ህጻኑን ይጎዳል፡፡ በእርግዝናዎ ወቅት የወባ በሽታ ባለበት ቦታ ነፍሰጡር ሆኖ አለመጓዝ እጅግ በጣም ይመከራል፡፡

መጓዝ ካለቦት፣ በእርግዝና ወቅት ለመውሰድ ደህንነታቸው የተጠበቁ መድሀኒቶች አሉ፡፡ ዶክተሮት ለእርሶ የበለጠ የሚስማማውን መድሀኒት በመምረጥ ያግዞታል፡፡



## የወባ በሽታ ምልክቶች ምንድናቸው? ካሉብኝ ምን ላድርግ?

የወባ በሽታ ምልክት ትኩሳት፣ መንቀጥቀጥ፣ ብርድ ብርድ ማለት፣ ራስ ምታት፣ የጡንቻ መዛልና ድካምን ያጠቃልላል፡፡ ጉንፋን እንደያዘት ሆኖ ሊሰማዎት ይችላል፡፡ የማቅለሽለሽ፣ ማስታወክ ወይም ተቅማጥ ሊኖሮትም ይችላል፡፡ ለእነዚህ ወዲያውኑ ህክምና ካልተገኘ የወባ በሽታ ሞትን ሊያስከትል ይችላል፡፡ ትኩሳት ወይም ጉንፋን-መሰል ህመም የሚሰማው ማንኛውም ተጓዥ ወደ ዶክተር ዘንድ መሄድ አለበት፡፡ በጉዞ ላይ ወይም ወደ ዩኤስ ከተመለሱ በኋላ በወባ በሽታ ሊታመሙ ይችላሉ፡፡ ከዶክተሮት የወባ በሽታ ያለባቸው አካባቢዎች እንደሄዱ ይንገሩና የወባ በሽታ ምርመራ ያድርጉ፡፡

በወባ መሽታ ላይ ለበለጠ መረጃ፣ www.cdc.gov ይጎብኙና 'malaria' ብለው ይፈልጉ፡፡

የሚጓዙበት አካባቢ የወባ በሽታ ስጋት ያለበት እንደሆነ ለማየት፣ www.headinghomehealthy.com ይጎብኙ፡፡

University of Minnesota

Department of Health

651-201-5414
www.health.state.mn.us

Amharic
9/2021